# የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 3 እና 4

1. ለምኑ ________ ፈልጉ____________ ደጅ ምቱ__________
ሀ)ይከፈትላችኋል፣ ይሰጣችኋል፣ ታገኛላችሁ
ለ) ይሰጣችኋል፣ ታገኛላችሁ፣ ይከፈትላችኋል
ሐ) ይከፈትላችኋል፣ ታገኛላችሁ፣ ይሰጣችኋል
መ) ይሰጣችኋል፣ ይከፈትላችኋል፣ ታገኛላችሁ

2. እግዚአብሔርን ብንለምን መልካም ስጦታን እንደሚያደርግልን ለማስተማር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ምሳሌን ተጠቀመ?
ሀ)ወዳጁን በሌሊት እንጀራ የጠየቀ ሰውን
ለ)ለልጁ መልካምን የሚያደርግ ወላጅ
ሐ)እንጀራን የሚያበረክት ሰው
መ)ሀ እና ለ

3. በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ያሉት መቼ ነበር?
ሀ)ደንቆሮ እና ዲዳ የነበረውን ሲያድን
ለ)አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሳ
ሐ)ሌጌዎን የተባሉት አጋንንትን ሲያወጣ
መ)ሁሉም

4. ጌታችንን ምን የሚል የአጋንንት አለቃ ስም ከፀሀፍት ፈሪሳውያን ተሰጥቶት ነበር?
ሀ)ዳጎን ለ) ብዔል ዜቡል ሐ) ገብርሔር መ) ሁሉም

5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አጋንንትን የማወጣው በምንድን ነው አለ?
ሀ)በብዔል ዜቡል
ለ)በመላእክት እርዳታ
ሐ)በእግዚአብሔር ጣት
መ)ሁሉም

6. ለነነዌ ሰዎች ምልክት የሆናቸው ነቢይ ማን ነው?
ሀ)ነቢዩ ዮናስ ለ)ነቢዩ ኤርሚያስ ሐ)ነቢዩ ኤልሳዕ መ)ነቢዩ ኤልያስ

7. የፈሪሳውያን እርሾ ተብሎ የተጠቀሰው ምንድን ነው?
ሀ)ቅንነት ለ)ንፁህ ልብ ሐ)ግብዝነት መ)ሀ እና ለ

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንን እንድንፈራ አስተማረን?
ሀ)ስጋን የሚገድሉትን ሰዎች
ለ)ነፍን ወደ ገሃነም ሊጥል የሚችለውን እግዚአብሔር
ሐ)የምድር ነገሥታትን
መ)ሁሉም

9. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ ስለምንበላው እንዳንጨነቅ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረበት ወቅት ምሳሌ ያደረገው እንስሳ የቱ ነው?
ሀ)ሰጎን ለ)ንስር ሐ)አንበጣ መ)የቁራ ጫጩቶች

10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ ለምድር ምን ይዞላት እንደመጣ ተናገረ?
ሀ)ሰላም ለ)ፍቅር ሐ)ውሀ መ)እሳት

11. ሐዋርያት ጸሎት አስተምረን ያሉት ከማን ተመልክተው ነው?
ሀ) ከመጥምቁ ዮሐንስ ለ) ከፈሪሳውያን ሐ) ከዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ መ) ሀ እና ለ

12. በፍርድ ጊዜ ከዚህች ትውልድ ጋር ይፈራረዳሉ የተባሉ እነማን ናቸው?
ሀ) የነነዌ ሰዎች ለ) ንግሥተ ዓዜብ ሐ) ሰዶም እና ገሞራ መ) ሁሉም ሠ) ሀ እና ለ

13. ጌታ ጸሐፍትና ፈሪሳውያንን ከገሰጸበት ነገሮች መካከል የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ሰውን ጽኑ ሸክም ያሸክማሉና
ለ) የተነገረውን ትንቢትና የተቈጠረውን ሱባኤ ዐውቀው ሰውረዋልና
ሐ) ግብዞች ነበሩና
መ) ሁሉም

14. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ የባለጸጋው ሰው ታሪክ ምሳሌነቱ ምንድን ነው?
ሀ) ባለጸጋው የአዳም፣ የሰበሰበው ገንዘብ የባሕርይ አምላክነት
ለ) ባለጸጋው የመላእክት ፣ የሰበሰበው ገንዘብ የባሕርይ አምላክነት
ሐ) ባለጸጋው የሙሴ፣ የሰበሰበው ገንዘብ የመንግሥተ ሰማያት
መ) ሀ እና ሐ

15. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ ከተባሉ መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ብዙ ከሰጡት ብዙ ይሹበታል
ለ) እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ስለሚያውቅ ምንም መሻት መጸለይ አያስፈልግም
ሐ) የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፣ ... ሁሉ ይጨመርላችኋል
መ) የጌታውን ፈቃድ ዐውቆ የማይሠራ እንደ ፈቃዱም የማያደርግ ፍዳው ብዙ ነው

16."በምድር ላይ እሳትን አምጥቼአለሁ፤ እርስዋን ከማንደድ በቀር ምን እሻለሁ?" እሳት የተባለች...
ሀ) ልጅነት ለ) ሃይማኖት ሐ) ዘረኝነት መ) ሀ እና ለ

17."ከእንግዲህስ ወዲህ አምስት ሰዎች በአንድ ቤት ቢኖሩ ሦስቱ ከሁለቱ፥ ሁለቱም ከሦስቱ ይለያሉ፤" ሲል አምስቱ የተባሉ ምንድን/እነማን ናቸው?
ሀ) ሐሳዊ ኤልያስ፣ ሐሳዊ ኤልሳዕ፣ ሐሳዊ አብድዩ፣ ሄኖክ፣ ኤልያስ
ለ) አራቱ ባሕርያተ ሥጋ፣ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስ
ሐ) ኃጢአት፣ ሰውነት፣ ሰይጣን፣ ነፍስ፣ መንፈስ ቅዱስ
መ) ሁሉም

18.ጌታ ስለ ዕርቅ የተናገረው የቱ ነው?
ሀ) የተጣላኸውን ሁሉ በሕግ፣ በዳኛ ተፋረድ
ለ) ወደ ዳኛ እንዳያደርስህ ከባለጋራህ ጋር በመንገድ ታረቅ
ሐ) ዳኛው ካለአዘዘ በቀር የምትከፍለውን አተስጥ
መ) ሁሉም

19."ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁ የበራ ይሁን።" ሲል
ሀ) በአማረ በአሸበረቀ ልብስ አጊጡ ሲል ነው
ለ) የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ ሲል ነው
ሐ) ወገብን መታጠቅ እና ብዙ መብራት ማብራት ለነፍስ ድኅነትን ያሰጣል ሲል ነው
መ) ሁሉም

20. "ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይሹታልና" የተባለው...
ሀ) ምግብ ለ) መጠጥ ሐ) የእግዚአብሔር መንግሥት መ) ሀ እና ለ